# <u>ምትክ ስያሜ በአማርኛ</u>

ማረው አለሙ

ማህበረሰብ በቋንቋ በሚገባ እንዲገለገል የሚያስችለው የቋንቋ ሰዋሰዋዊ <u>ህግጋት</u> ብቻ አይደለም። ከዚህ በላይ የሥነልሣናዊ ሥነምግባር ዕውቀት በጣም ያስፈልገዋል - ማን፥ ምን፥ ለማን፥ እንዴት መናገር እንዳለበት የሚያስችለው የቋንቋ ሥነምግባራዊ ችሎታ ያስፈልገዋል። የቋንቋው ተጠቃሚ በሚጠይቀው ማህበራዊ ደንብ መሠረት የንግግርንና የድምጡትን ጊዜ መለየትንና ምን፥ ለማን፥ እና እንዴት መናገርን ማወቅ አለበት። በቋንቋው "በትክክል" ተገለገልኩ ማለት የሚችለው ከቋንቋው የአወቃቀር ሥርዐት በተጨማሪ እነዚህን የአጠቃቀም ባህሪያት ለይቶ በአግባቡ ሲጠቀምባቸው ነው (Cooper 1976: 567)። በአጠቃላይ የቋንቋውን የመግባቢያ ደንብ ማወቅ ያስፈልጋል - በቋንቋው ለመጠቀም።

ቋንቋ በራሱ ባህል ከመሆን አልፎ የባህልም ገላጭ በመሆኑ፥ ባህል የሚያደርስበት ተፅዕኖ አለ። ከተጽእኖው አንዱ <u>ነውር</u> እየተባለ የሚጠራው የቋንቋ አጠቃቀም ዘርፍ ነው። ከቋንቋ አንፃር ሲታይ ነውር፥ የማይባል ወይም የማይጠራ ቃል ወይም የተወሰኑ ቃላትና አገላለጾች ይፋ እቀባ ማለት ነው። እንደነዚህ ያሉ ቃላትና አገላለጾች ህብረተሰቡ በይፋ ስለማይጠቀምባቸው ህልውናቸው አጠራጣሪ ነው (Trugill 1974: 29) ።

ነውርነት የማህበራዊ ደንብ ውጤት ነው። በማህበራዊ ደንቡ ምክንያት ይፋ የማይወጡ ድርጊቶች፥ ቁሶችና ስያሜዎች አሉ፤ ቋንቋው አጠይሞ ወይም አስታሞ የሚገልፃቸው፥ ለተጠቃሚው ሙሉ ነፃነት የማይሰጡ። የደስታ ተክለ ወልድ <u>ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት</u> "ነውር በሰው፥ በእንስሳ ገላ ላይ ያለ ዕብጠት፥ ጉድለት፥ ለአይን የሚያስቀይም፥ ክፉ ግብር፥ ኃጢአት፥ ስካርን፥ ምንዝርን የመሰለ" በማለት ይገልፀዋል /1962፡ 847/። ይህም ነውር አስቀያሚ፥ አስፈሪና አሳፋሪ ባህሪ እንዳለው ያስገንዝባል።

ስፋትና ጥበቱ፥ ልልነትና ጥብቀቱ ወይም ጠቅላላ ባህርይው እንደየባህሉ ቢለያይም የነውር እሳቤ ግን በማንኛውም ቋንቋና ባህል ተመሣሣይ ነው። በይፋ አለማድረግ፤ አለማየት ወይም አለመታየት፥ አለመጥራት ወይም አጠይሞ መግለፅን ነው የሚያመለክተው። በሌላ አባባል የቁሱ፥ የድርጊቱና የስያሜው ምስጢራዊ ተለምዶ የሚጠበቅለት ማለት ነው። በባህርይው ባህላዊ፥ ሃይማኖታዊና ማህበራዊ ከለላን ስለሚይዝ፥ የድርጊት፥ የእይታና የአንደበት ይፋነቱ ውጉዝ ወይም ክልክል ነው - ፀሐይ የማይሞቀው፥ ከሩቅ የሚሸሹት ዓይነት።

ነውር በሰው፥ በቦታ፥ በቁስ ወይም በድርጊት የሚከሰት ቢሆንም ከሁሉም ይልቅ ሃይማኖታዊ ከለላነቱ ይጠነክራል። ማንኛውም ሃይማኖት በተከታዮቹ የሚጠበቅና የሚከበር ነውር አለው። ይህን ተለምዶ የጣሰ ቡድን ወይም ግለሰብ "በበሽታ፥ በሞትና በሌላም መጥፎ እድልና አጋጣሚ እቀጣለሁ" የሚለው እሳቤ ሁልጊዜ በአዕምሮው ስላለ፥ ነውሩን ለመጠበቅ ሲበዛ ጥንቁቅ ይሆናል። ነውር በአብዛኛው ማህበራዊ፥ ሃይማኖታዊና ባህላዊ መሠረት ያለው አይደፈሬ ልማድ ነው የሚባለውም ለዚህ ነው - የአንድ ነገር ይፋነት ክልል እስከየት ድረስ እንደሆነ በግልፅ ያሳያልና።

ነውር ሃይማኖታዊ ብቻ ሳይሆን ማህበራዊ እቀባም አለው:: የነውርን ምስጢራዊነት አለመጠበቅ እንደየባህሉ ሁኔታ በማንኛውም መልኩ የሚያደርሰው ማህበራዊ አደጋ እንዳለ ጥናቶች ይጠቁማሉ:: ከፍ ሲል የተጠቀሰው ትራጅል የተባለው የሥነልሣን ተመራማሪ /1974: 87/ በዙሉ (ደቡብ አፍሪካ) ብሔረሰብ ሴት የባሏን አባት በተፀውኦ ስሙ መጥራት እንደማትችልና ከጠራች ግን በሞት እንደምትቀጣ የዘገበው ለአብነት ይጠቀሣል:: በኛም ሀገር በሲዳሞ ህብረተሰብ ተመሳሳይ ሁኔታ አለ፤ (አንበሳ 1987'ን ይመልከቱ):: በሌላው አካባቢም ነውርን መጣስ ለሞት ባያደርስም የተለያዩ ማህበራዊ እቀባዎችን ያስከትላል:: እንደማውገዝ÷ ማጋዝ÷ ተሰሚነት ማጣት÷ ማግለል÷ ወዘተ. ... ከማህበራዊ እቀባዎቹ ውስጥ ጥቂቶቹ ናቸው:: ስለዚህ ነው ማንኛውም ጤናማ ሰው ማህበረሰቡ የሚያከብረውንና ከነውር የሚጠብቀውን ነገር እንዲያከብር የግድ የሚሆንበት:: ከዚህ ላይ ግን ማስተዋል ያለብን ነውር "ይህን አድርግ÷ አታድርግ÷ በል - አትበል" ተብሎ በህግ የተደነገገ ሣይሆን÷ ማህበራዊ ደንብ ብቻ የሚከለክለው ነገር መሆኑን ነው:: እናም ሰዎች ከአደጉበት ማህበረሰብ የሚካፈሉትና የሚለምዱት ይሆናል - በማየት÷ በመስማትና የድርጊቱ ተሣታፊ በመሆን:: የሥነልቦና ጥናት እንደሚያስረዳው÷ ማንኛውም ጤነኛ ህፃን ከአምስት አመት በፊት ጾታ የመለየትን እሳቤ ያዳብራል:: ራሱን ከተባዕታይ ወይም ከአንስታይ ጎራ የሚመድብበት ግንዛቤ ይኖረዋል:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ልምዱና ገጠመኙ እየሠፋ በሄደ ቁጥር ምን ዓይነቱ ጠባይ እንደሚያስቀጣ÷ ምን ዓይነቱ እንደሚያስወድድ ወይም እንደሚያስመሰግን÷ የትኛው ዓይነት ባህሪ የሥነምግባር ብልሹነት ወይም ሠናይነት ስም እንደሚያሰጥ÷ የትኛው ደግሞ እንደሚያስከብር ወዘተ... ከእድሜ እኩያዎቹና ከወላጆቹ በአጠቃላይ ከማህበረሰቡ ይማራል:: የጾታ ልዩነት ግንዛቤውን እያዳበረ ሲሄድም እግረ መንገዱን በቀጥታ ወይም በግልፅ ድርጊታዊ ተሣትፎ ሣይሆን÷ ብዙውን ጊዜ አእምሮአዊ ንቃት ባልተላበሰ መግባባት ቀስ በቀስ ወሲባዊ ገጠመኙን ያሣድጋል:: ማንም ህፃን ከጉልበት በላይና ከወገብ በታች ካሉት በስተቀር የራሱን ወይም የሌላውን የሰውነት ክፍሎች በይፋ መንካትና ማሣየት እንደሚቻል የሚማረው በዚሁ ሁኔታ ነው:: እነዚህን ክፍሎች በግልፅ መንካት ወይም መዳበስ እንደሚቻል ሲገነዘብ በተዘዋዋሪ ይፋ የማይሆኑ የሰውነት ክፍሎችንም ይለያል:: ምክንያቱም ህፃኑ ህፍረተ-ስጋውን በይፋ ሲደባብስ በአዋቂዎች ሲታይ ተቀባይነትን ከማሳጣት አልፎ ግሣጼና ግርፋትም ስለሚያስከትልበት ቀስ በቀስ ክልክል (ነውር) የሆኑ ነገሮችን በይፋ ላለማሣየት÷ ላለማየትና ላለማድረግ "እርም" ብሎ ይተዋል:: እነዚህ የህፍረተ-ሥጋ ነውሮችም በህፃኑ የመፀዳዳት ሥራ ላይ ከባድ ተፅዕኖ ስለሚያሳድሩ ቦታና ጊዜ የሚመረጥላቸውን የመፀዳዳት ተግባራት እግረ መንገዱን ይማራል:: <u>ተፈጥሮን መቆጣጠር መቻሉ</u> የሚያስከብረውና ምግባረ-ሠናይ የሚያሰኘው መሆኑንና ይህን ሣይችል ቀርቶ ግን <u>ተፈጥሮውን</u> እንደመጣ በማንኛውም ጊዜና ቦታ የሚያስተናግድ ከሆነ÷ ተቀባይነትን ማጣት÷ ጥላቻን ማትረፍና በጠቅላላው ከሰው ተራ አለመዋልን እንደሚያስከትልበት የሚረዳው ነውር ከሚባሉት የሰውነት ክፍሎች ነው:: በሌላ አገላለፅ÷ ህፃኑ ነውር ከሆነ ነገር የሚወጣ ማንኛውም ፈሣሽ ወይም ጠጣር ነገር እንዲሁ ነውር መሆኑን ይማራል ማለት ነው:: ስለዚህ ነውር ከሚባሉ የሰውነት ክፍሎች በቆሻሻ መልክ የሚወጡ ነገሮችን ጊዜና ቦታ ለይቶ ማስወገድ የእይታና የአንደበት <u>ህቡዕነታቸውን መጠበቅን</u> ህፃኑ ከአደገበት ማህበረሰብ በመማር በጤና እስካለ ድረስ በቋሚነት የሚጠብቀው ጉዳይ ነው::

በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ ያሉትን የነውር ቃላት በአምስት ዋና ዋና ክፍሎች መመደብ ይቻላል:: እነዚህም የሚከተሉት ናቸው::

ክብር
ፍራቻ
ጥየፋ/ጥላቻ
ምላስ አድጥና
ነውር መሰል

ተናጠላዊ ትንታኔያቸውን ቀጥለን እንመለከታለን::

2.1 ክብር: የአማርኛ ቋንቋ ተጠቃሚ ከእምነቱ ወይም ከሃይማኖቱ ጀምሮ በርካታ ነገሮችን ያከብራል:: ጋብቻ፥ ልደት፥ ዓመት በዓል፥ ወላጆች፥ ታላላቅ ሰዎች፥ የሃይማኖት አባቶችና የመሣሠሉት በቋንቋው ተጠቃሚ ህብረተሰብ ዘንድ ልዩ ክብር ይሰጣቸዋል:: እነዚህን አስመልክቶ ማህበረሰቡ በቋንቋው ምንና እንዴት እነደሚናገር እንመልከታለን::

2.1.1. ሃይማኖት: የኦርቶዶክስን ሃይማኖት ለአብነት እንውሰድ:: የዚህ ሃይማኖት ተከታዮች ለሃይማኖቱ ካላቸው ፍርሃታዊ ፍቅርና አክብሮት የተነሣ ሃይማኖቱንና ሥርዐታዊ ስያሜዎችን በይፋ አይጠሩም - በተተኪ ቃላት እንጂ:: ለምሳሌ ለቁርባን ሥጋወደሙን፥ ለታቦት ፅላትን፥ ለሰንበት ቂጣ/ዳቦ/ መክለፍትን፥ ለቤተክርስቲያን መሣም ወይም ለመሣለም እጅ መንሣትን፥ ለማስቀደስ ማስቆረብን፥ ለመፀለይ ሱባዔ መግባትን ይመርጣሉ:: ቀጥተኛ ስያሚዎችን በምትክ ቃላት ከመጥራት በተጨማሪ ስለብዙዎቹ ሃይማኖታዊ ሥርዐቶች በዝርዝር መነጋገርም በጣም ነውር ነው:: ለምሳሌ ሥጋወደሙ ስለሚባለው ጉዳይ ሥነሥርዐቱ ምንድን ነው? የሚል ጥያቄ ቢነሳ መልስ የለውም:: በቀሣውስቱ ብቻ በምስጢር የሚያዝ ሥርዐት ነው:: በዚሁ ሃይማኖት ሥርዐት ውስጥ ከሚዘወተሩት ጉዳዮች አንዱ ማንኛውንም ነገር ከማድረግ በፊት 'በስመአብ...' የሚለውን ቃል መጥራት ነው:: ለምሣሌ ምግብ ሲቀርብ፥ ሴት ከጎተራ እህል ስታወጣ ወዘተ... ይህን ቃል ማስቀደም በሃይማኖቱ ተከታዮች ዘንድ በጣም የተለመደ ነገር ነው:: ሆኖም ከአመት ውስጥ ይህን ቃል መጥራት ነውር የሚሆንበት አንድ ወቅት አለ - ሰሞነ ህማማት:: በዚህ ሣምንት በስመአብ የሚለውን ቃል መጥራት ነውር ስለሆነ በምትኩ ኪራላይሶ ይባላል::

ለሃይማኖቱ ከፍተኛ ክብር ከመስጠት አንፃር የሃይማኖት አባቶችም ከፍተኛ ግምት ይሰጣቸዋል:: በተፀውኦ ስማቸው አይጠሩም:: ለብዙዎቹ 'አባታችን' የሚለው ቃል የጋራ መጠሪያቸው በመሆን ያገለግላል:: በተፀውኦ ስማቸው መጥራት ነውር ነው::

2.1.2. ጋብቻና ልደት: "ወልደህ ሣም ዘርተህ ቃም"፥ "የተናገሩት ከሚጠፋ የወለዱት ይጥፋ"፥ "የወለዱትን ካልሣሙለት...ወዘተ...." የሚሉት አባባሎች ጋብቻና ልደት በማህረሰቡ ዘንድ ልዩ ክብር የሚሰጣቸው መሆኑን ያስገነዝባሉ:: እናም በመውለድና በዙሪያው ያሉት ነገሮች በቀጥተኛ ስያሜያቸው አይጠሩም - እንደነውር ይቆጠራሉ::

ስለዚህም ወለደች ለሚለው ተገላገለች፥ ራሷን ተካች፥ የማርያም አራስ ሆነች፤ አርግዛላች ለሚለው ፀንሳለች፥ ነፍሰጡር ነች፥ ቅሬት ነች፤ አደፍ ለሚለው የወር አበባ እያሉ ለተሰያሚው ተተኪ ስያሜ በመስጠት በተተኪ ቃላት ይጠቀማሉ። ጋብቻም እንደዚሁ የራሱ የሆኑ አሉት። አገባች ከማለት መቀነቷን ፈታች፥ ጉልቻ መሠረተች፥ ትዳር ያዘች፤ ባል ወይም ሚስት ከማለት ባለቤት ማለት የተለመደ ነው።

2.1.3. አካላት፡ ከወገብ በታች፥ ከጉልበት በላይና፥ በጉልበት መካከል የሚገኙት የሰውነት ክፍሎች ከሌሎች የተለየ ጥበቃ ይደረግላቸዋል። ሆድን፥ ደረትን፥ ጀርባን፥ አንገትን ለሌላው ሰው በይፋ ማሣየት ይቻላል። እነዚያን ግን ምናልባትም ለሃኪም ካልሆነ በስተቀር ለሌላ ሰው በግልፅ ማሳየት በጣም ነውር ነው። በስማቸው አይጠሩም በጥቅሉ ሀፍረተ ሥጋ ወይም ብልት በሚል ተተኪ ስያሜዎች ይጠራሉ። በዝርዝር ሲታዩ በርካታ ናቸው። ቂጥ ከማለት መቀመጫ፥ _____ ከማለት ግንድ፥ የዘር መዝሪያ _____ ከማለት ፍሬ፥ _____ ከማለት የሴት ብልት ማለትን ተጠቃሚው ይመርጣል።

ከዚህ ሌላ በተለይም በእንቆቅልሽና፥ በሌሎች የሥነቃል ዘርፎች እነዚህን አስመልክቶ የተለያዩ ተተኪ ቃላት ይዘወተራሉ። የሁለት ሰዎችን ውይይት ለአብነት እንመልከት፥

የምስራች "ሚስቴ ወለደች?" ይላል ነጋሪ
"ምን ወለደች?" አድማጭ
"ሁለቱንም ወለደች።" ነጋሪ
"አንተ አንድ ስትሆን ሁለት
"መውለድህ በምን ምክንያት
" ነው?" አድማጭ
"ግንዱ አንድ ቢሆን
ፍሬው ሁለት አይደለም ወይ?" ነጋሪ
(የካቲት መጽሔት 1983፥ ቁ. 7፥ ገጽ 36/

እላይ በተመለከትነው ምልልስ ውስጥ ሁለት ቃላት (ግንድና ፍሬ) የነውሩን ምስጢራዊነት ለመጠበቅ ወይም ለመሸፈን ሲባል የገቡ ተተኪ ቃላት መሆናቸውን እንገነዘባለን።

እንቆቅልሽ ነገሮችን ደብቆ፥ የሰውን አእምሮ ከሚፈታተንባቸው ነገሮች መካከል ብዙዎች በሰውነት አካላት በተለይም ነውር በሚባሉት ላይ የተመሠረቱ ናቸው። የሚከተሉትን ምሳሌዎች ለአብነት እንመልከት።

ምሣሌ 1 ራስ-መላጣ ሁለት ልጆች ይዞ ከዱር የሚወጣ÷[*]

በዚህ እንቆቅልሽ ውስጥ ሶስቱ የተሰመረባቸው ሀረጎች በይፋ የማይጠሩ ነገሮችን ተክተው የገቡ ናቸው:: ራስ መላጣ የግንዱ ጫፍ÷ ሁለቱ ልጆች ፍሬዎቹ ሲሆኑ÷ ዱሩ ደግሞ በብልት ዙሪያ የሚገኘውን ተፈጥሮአዊ ፀጉር ያመለክታል::

ምሣሌ 2 ሶስት ወንድማማቾች ሲሮጡ፤
አንዱ ገደል ገባ ሁለቱ አመለጡ::

ሶስት ወንድማማቾች የተባሉት ግንዱና ሁለቱ ፍሬዎች ናቸው:: ገደሉ ሩካቤ ስጋ ነው:: ገደል የገባው ግንዱ ሲሆን (በሩካቤ) ያመለጡት ደግሞ ፍሬዎቹ ናቸው:: ተፈጥሮአዊ ግዴታ የሆነው የጾታ ግንኙነት ከነክብሩ የተገለፀበት እንቆቅልሽ ነው ለማለት ይቻላል::

ምሣሌ 3 ከአንድ ባላ ሁለት ቅሎች ተንጠልጥለው÷

በዚህ ውስጥ ደግሞ ባላው ግንዱ ሲሆን÷ የተንጠለጠሉት ቅሎች ፍሬዎቹ ናቸው::

ምሣሌ 4 ሲሄድ እየፎከረ ሲመለስ እያለቀሰ÷

ሲሄድ የሚፎክረው ግንዱ ሲሆን÷ ሲመለስ ማልቀሱ ደግሞ ከሩካቤ በኋላ ያለውን ሁኔታ የሚያሳይ ስዕላዊ መግለጫ ነው::

ምሣሌ 5 ሸህ ዘካርያ ቆላ ያሉት÷
ጥቁር ካባ ነው የለበሱት÷
ሁለት ደረሶች ያስከተሉት÷
ሀድራውን ገብተው ነስነሱት÷
ነጭ ማር ተፍተው የሚወጡት÷

ይህ እንቆቅልሽ ይፋነታቸው በከፍተኛ ደረጃ አሳፋሪ የሆኑትንና በጥቅሉ ሀፍረተ ሥጋ የሚባሉትን ከአምሣላቸው እስከ ግብራቸው ድረስ በዝርዝር የሚያሣይ ነው:: ሸህ ዘካሪያ በሚል በአክብሮት የተጠራው የወንድ ብልት ግንድ ሲሆን÷ ካባ በዙሪያው ያለውን ፀጉር÷ ሁለቱ ደረሶች ፍሬዎቹ ሲሆኑ ሀድራው የብዕሲትን ነውር አካል ብልት ያመለክታል:: ነጭ ማር የተባለው የሩካቤውን ተፍፃሜትና ውጤት የሚገልጽ ነው::

ምሣሌ 6 ቀይ ስልቻ÷
የሞንዳሌ መክተቻ÷

እንቆቅልሹ የአንስታይን ነውር አካል ይመለከታል:: 'ቀዩ ስልቻ' የብዕሲት ሲሆን 'ሞንዳሌ' ደግሞ የወንድ ብልት ነው::

---

[*] በዚሁ ጽሑፍ ውስጥ አይጠሬ የሆኑ ነገሮች በሰረዝ ተመልክተዋል::

ምሣሌ 7 በፀጉር የተከበበች ገደል፥

ይህም ከላይኛው ጋር ተመሣሣይነት አለው:: የብዕሲትን ህፍረተ ሥጋና በዙሪያው ያለውን ፀጉር ያመለክታል::

በአጠቃላይ እንቆቅልሽ ነገሮችን ደብቆ የመግለፅ ባህሪ አለው:: በአብዛኛው የሚመረጡት ድብቅና ከሰዋኅት አካላት አይነኬና አይጠሬ የሚባሉት እንደሆኑ እስካሁን ከቀረቡት ምሣሌዎች መገንዘብ ይቻላል:: በምልልሱ ውስጥ ተጠያቂው ነውሩን የመጣስ አዝማሚያ ይታይበታል:: ይህ ግን በእንቆቅልሽ ብቻ ሣይሆን በአጠቃላይ ትውፊት ውስጥ የሚዘወተር ተግባር ነው:: በዘፈን፥ በቀረርቶ፥ በፉከራ፥ ወዘተ... ነውር ሲጣስ ይታያልና::

2.1.4. ወሲብ: ከፍ ብሎ ያየናቸው የሰውነት አካላት አይጠሬነታቸው እንደሚጠበቅ ሁሉ በእነሱ አማካይነት የሚፈጸመው ሰብአዊና ተፈጥሮአዊ የጾታ ግንኙነትም የተለየ ግምት ተሰጥቶት እንደዚሁ አይጠሬ ነው:: ለምሳሌ ______ለማለት 'ተራከባት'፥ 'ተገናኛት'፥ 'ተጫዎታት'፥ 'ተኛት'፥ 'ደፈራት'፥ 'አወቃት'፥ 'ተዋሰባት'፥ 'ተዋደቃት' ሲባል የሚሰማው የወሲብን ድብቅና ምስጢራዊ ድርጊት ከፍተኛ ጥንቃቄ በተሞላበት አጠቃቀም በተተኪ ቃላት ለመግለፅ ነው:: ለዚህ አቶ መንግሥቱ ለማ ከጎንደር ገበሬ የሰማሁት ብለው የጠቀሱትን ቃላዊ ግጥም ተጨማሪ ምሣሌ አድርገን እናቀርባለን::

በትንሽ ጎጆ ትንሽ ቁሮንጮ ትነጠፍና
እህ ዛዲያማ?
እህ ዛዲያማ፥ ምን ልበላችሁ
ታውቁት የለም ወይ በየቤታችሁ?
(መንግሥቱ ለማ፥ 1963፥133)

ግጥሙ በጣም የሚያጓጓና ልብን የሚሰቅል አቀራረብ አለው:: በማጓጓቱ ሂደት ፍራቻም ያጭራል:: 'ነውሩ ይጣስ ይሆን?' የሚል ጥያቄም ያስነሳል:: ግን መጨረሻ ላይ ያለው ስንኝ ሁሉንም ያረጋጋል::

ካንተ ተኝታ ሌላ ታማራት፥
በል ተነሥና በዱላ በላት፥

ይህም ቃላዊ ግጥም ለነገሩ ድብቅነት ምን ያህል መቸገር እንደሚያስፈልግ ለአብነት የሚጠቀስ ነው:: በግጥሙ ውስጥ ነውሩን ደብቆ የያዘው ቃል 'ተኝታ' የሚለው ሲሆን፥ በርካታ ነውራዊ ድርጊቶችን ያሣሥባል::

እስካሁን ያየናቸው ቃላዊ ግጥሞች ነውር ደባቂ የሆኑ ተተኪ ቃላት ያላቸው ናቸው:: ነውሩን በመጣስ የሚቀርቡና በድፍረት የሚባሉ እንዳሉ ግን መዘንጋት የለበትም:: ምናልባትም ግጥሞቹ የህዝብ በመሆናቸው አንድን ሰው በተለይ ነውረኛ ወይም ባለጌ ሊያሰኙ ስለማይችሉ ይሆናል::

እሜቴ ይመቱ እኔ ነኝ ልጅዎት
ከእምብርትዎ በታች ልጎልምብዎት /ልፈልምበዎት/
ከእምብርቴማ በታች_______ አይደለም ወይ?
አንተ የባለጌ ልጅ_______ ነው ወይ?

ይህን ግጥም ከአንደበቱ የሚያወጣ ሰው በነውርነታቸው ምክንያት ለማይጠሩ ድርጊቶችና የሰውነት ክፍሎች አልተጨነቀም:: ምናልባትም በጊዜው በሚፈጠረው የጨዋታ ሁኔታ ተደፋፍሮ ሊሆን ስለሚችል የነገሮቹና የድርጊቶቹ መጠራት ብዙም ላያሳስበው ይችላል::

2.1.5. <u>ሥርዐተ አጠራር</u>: በአማርኛ ቋንቋ ተጠቃሚዎች ዘንድ በዕድሜ ገፋ ያሉ ሰዎች፥ የሃይማኖት አባቶች፥ የተማሩ ሰዎች፥ አባት፥ እናት፥ አማት፥ ታላቅ ወንድምና እህት፥ ወዘተ... የአክብሮት መጠሪያ አላቸው:: አክብሮቱም ሁለት ዓይነት ነው:: አንደኛው አንቱታ ሲሆን ሁለተኛው ከተፀውኦ በተለየ ስም በመጥራት ነው:: ተማሪው መምህሩን 'ጋሼ' ወይም መምህር (የቤተክህነቱን ደግሞ 'የኔታ') ሲል፥ ልጆች ወላጆቻቸውን አባዬ፥ እማዬ ከማለት አንስቶ ሌላ ስም አውጥቶ እስከመጥራት ይደርሣሉ:: በአብዛኛው አያትና ቅድመ አያትን ጨምሮ በዋና ስም መጥራት ነውር ነው:: የሃይማኖት አባቶች <u>አባታችን</u>፥ አባ፥ ብፁነታቸው ወዘተ... በሚል ልዩ ስያሜ ይጠራሉ:: መነኮሣትም <u>አባ ሆይ፥</u> <u>እማሆይ</u> የሚል የአክብሮት መጠሪያ አላቸው:: <u>አማት</u> ወደሚባለው የዝምድና ደረጃ ስንመጣ ደግሞ አክብሮቱ ጠበቅ ያለ ሆኖ እናገኘዋለን:: ሴት የባለቤቷን አባትና እናት፥ ወንድም እንዲሁ የሚስቱን አባትና እናት በከፍተኛ ደረጃ ማክበር ይጠበቅባቸዋል:: ከዚህም የተነሣ ወንድ አማቱን <u>እሜቴ፥ የኔታ</u> ሲል፥ ሴት ደግሞ ልጆቻቸው ባወጡላቸው ወይም ራሷ ባወጣቸው ስም ትጠራለች እንጂ አማቶቿን በስማቸው ደፍራ አትጠራም:: ይህ በተለይ በገጠሩ አካባቢ ጥብቅ ስርዓት ነው::

በባልና በሚስት መካከል ያለውን ሥርዐተ - አጠራር ስናስተውል ደግሞ በተለይ ሚስት ባሏን በዋና ስሙ እንደማትጠራ እንገነዘባለን:: አልፎ አልፎ ለባላቸው ስም የሚያወጡ ሚስቶች ሲኖሩ፥ በአብዛኛው ግን <u>እሱ</u> ወይም እርሳቸው በሚል ተውላጠ ስም ይጠቀማሉ:: ልጅ ከወለዱ በኋላ ግን ለምሣሌ ባለቤቷን ሚስት አባትሽን ወይም አባትክን ጥሪው/ጥራው በማለት በልጆቿ ታስጠራለች:: አለበለዚያም የ'እገሌ' አባት በማለት በአባትነቱ ትጠራለች::

ከአማቷና ከባለቤቷ በተጨማሪ በዕድሜ ለሚበልጧት የባሏ ወንድሞችና እህቶችም የአክብሮት አጠራር አላት:: በዋና ስማቸው አትጠራቸውም:: ሌሎች ወንድሞቻቸው/እህቶቻቸው ባወጡላቸው ስሞች ትጠራለች እንጂ:: ይህ ካልተቻለ የራሷን ስም ታወጣለች:: ለእሷም እንደዚሁ ስም ያወጡላታል:: የስም አወጣጡ ከባለቤቷ ወላጆች ጀምሮ ወንድሞቹን እንዲሁም ጎረቤትንና ሌሎች አዝማዶችን ይጨምራል:: ሁሉም የተለየ ስም ያወጡለታል::

እስካሁን የተመለከትናቸው ምትክ ስያሜዎች የሚያስገነዝቡት ሰዎች ርስበርስ ካላቸው ግንኙነት የተነሣ በማህበራዊ ደንብ አስገዳጅነት መከባበር መተፋፈር ያለባቸው መሆኑንና በዚህም ምክንያት በምትክ ስያሜ እንደሚጠቀሙ፥ ይህን ባያደርጉ ባለጌ፥ እብድ፥ ወፈፌ፥ ነገሩ ከሰው የማይገጥም፥ ምግባረ ብልሹ ወዘተ... እንደሚባሉ ተገንዝበናል። ሆኖም ግን ምትክ ስያሜዎች በሁሉም አካባቢ ተመሣሣይ አለመሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል። በተለይም በገጠርና በከተማ መካከል እንደሌላው ነገር ሁሉ የምትክ ስያሜ አጠቃቀም ልዩነት ሰፊ ነው። በገጠር ነውር የሚባሉት በከተማው ከፊል ነውር ወይም ፈጽሞ ነውር ላይባሉ ይችላሉ። በከተማ አካባቢ ልጆች ወላጆቻቸውን በዋና ስማቸው ቢጠሩ ነውር አይደለም፤ በገጠሩ ግን ፈጽሞ ነውር ነው። በተለይም አዲስ አበባ አካባቢ ጎረቤታሞች የእገሌ አባት፥ የእገሊት እናት፥ እያሉ መጠራራት የተለመደ ሲሆን በብዙ ገጠር አካባቢዎች ግን በተፀውኦ ስምና እንደየሁኔታውም በአክብሮት መጠሪያ ካልሆነ 'የእገሌ አባት' ማለት ነውር ነው።

2.1.6. ምግብና መጠጥ፡ በአጠቃላይ ጣፋጭና ለሰውነት ጠቃሚ የሆኑ ነገሮች ይወደዳሉ፥ የሚወደድ ነገር ደግሞ በልዩ ስም ይጠራል። እናም በአማርኛ ቋንቋ ወተት ለማለት የላም ልጅ፥ ቅቤ ለማለት ወዝ፥ እርጎ ለማለት መንከሪያ፥ ጠላ ለማለት የአሰር ውሃ ወዘተ... ልዩ መጠሪያ ቃላት ናቸው። በተለይም ለወተት የሚሰጠው ልዩ ግምት ከፍተኛ ነው። እርጎ ለምግብነት ሲቀርብ እንደ ወጥ ተጋልጦ ሳይሆን፥ እላዩ ላይ ሽፈን የሚያደርግ እንጀራ ተጥሎበት ነው። በጥቅሉ እነዚህን እስካሁን ለአብነት የተጠቀሱትንና ሌሎች መሰል ጣፋጭና ጠቃሚ ምግቦች በመደበኛ ስማቸው ሣይሆን በተተኪ ስያሜ መገለጻቸው ህብረተሰቡ ለእነሱ የተለየ ግምት መስጠቱን ያመለክታል።

2.2 ፍራቻ፡ ሰው በህይወት ሲኖር የሚፈራቸው ነገሮች በርካታ ናቸው። ሞትን፥ መድሐኒትን፥ አውሬን፥ በሽታን፥ ድህነትን፥ በረዶን፥ ጦርነትን፥ ውሃ ሙላትን፥ ዛርን፥ ሰይጣንን ወዘተ...አጥብቆ ይፈራል። በዚህ ሰው ከሩቅ የሚሸሻቸው ብቻ ሣይሆኑ በቀጥታ ስማቸው የማይጠሩ ናቸው። አንዳንዶቹን በተናጠል እንመልከት፡

2.2.1. ሞት፡ ማንኛውም ሰው መኖር እንጂ መሞት አይፈልግም። ሞት አይቀሬ ቢሆንም ሰው በህይወቱ ከሚፈራቸው ነገሮች የመጀመሪያው ነው ለማለት ይቻላል። እናም ሞተ ከማለት አረፈ፥ አለፈ፤ ሰው ገደለ ከማለት እጅ አለፈበት፥ እጅ ሣተበት፥ ነፍስ ጠፋበት ወይም ነፍስ ወደቀበት፤ ሰው ገዳይ ከማለት ባለደም፤ ሬሣ ከማለት አስከሬን፤ ለቅሶ ከማለት ህዘን፤ አባቱ ሞተበት ከማለት አባቱን ተጎዳ፤ ማላቀስ ከማለት ማስተዛዘን ማለትን እየመረጠ ነው ህበረተሰቡ የሚግባባው። ሰይፉ መታፈሪያ ፍሬው ውስጠት (1981:74) በሚለው የሥነግጥም መደብላቸው በአንደኛው ሥነግጥም አስከሬንን ማንሜነት በማለት እንደሚከተለው ይገልፁታል።

'ማንሜነት'

ባንድ አግጣጫ መንገድ፥ ባንድ አግጣጫ ጎዳና
እስከ መሞቱ፥ እስከመበደኑ ሄደና
ያውና
ያው
ዕቃው
እንትኑ
በድኑ

ገጣሚው በግልፅ ወይም በቀጥታ ለመጥራት የፈሩት ነገር እንዳለ የሚያመለክቱ አገላለጾች በግጥሙ ውስጥ ይታያሉ:: ያውና ያው 'ዕቃው' 'እንትኑ' 'በድኑ'...እነዚህን የመሣሰሉት ቃላት አንድን ጉዳይ በቀጥታ ለመግለፅ የገቡ ቃላት አይደሉም - መሸፈኛ ወይም አጠይሞ መግለጫዎች ናቸው:: የመደበኛው ስያሜ ምትክ ናቸው::

ሞትና ሌሎችም አስፈሪ ነገሮች ብዙውን ጊዜ 'እንትን' በሚል ስያሜ እንደሚጠሩ ከሰይፉ መታፈሪያ ሥነግጥም በተጨማሪ ሌሎችንም መጥቀስ ይቻላል:: ለምሣሌ

"እንትናችን ውስጥ እንትን ገብቶበት
እንትን ላኪልኝ እንትን እልበት፥
አንችም ነይልኝ እንትን ትይልኝ"

የሚለው መልዕክት ሰውየው አንድ አስፈሪ ነገር እንደገጠመውና ራሱን እስከሚያዘጋጅ ድረስ ቀጥተኛ ስሙን መጥራት እንደተቸገረ ያመለክታል::

2.2.2. <u>በሽታ</u>: በሽታ ያሰቃያል፥ ያመነምናል፥ ብሎም ለሞት ይዳርጋል:: ስለዚህም ይፈራል:: ማህበረሰቡ ከበሽታ ዓይነቶች አንዱንም አይወድም - ይጠላል እንጂ - በቋንቋውም ሲገለገል <u>የጉበት በሽታ</u> ለማለት <u>ወፍ፤ ኩፍኝ</u> ወይም <u>ፈንጣጣ</u> ለማለት <u>አለሞቼ፤ ወተቴ</u>፥ <u>የቆዳ በሽታ</u> ለማለት <u>ክፉ ገላ፤ እብድ</u> ለማለት <u>በሰው የተዋለበት/ዕጀሰብ የቀመሰ</u>/፥ ኤድስ ከማለት አዲሱ ወይም <u>ዘመነ አመጣሹ በሽታ</u> በማለት የተለየ ስም ወይም አባባል እየመረጠ ሲጠቀም ይታያል:: ነውሩ ግን ከበሽታው ዓይነት ብቻ ሣይሆን ከመፈወሻ መድሐኒቱም ላይ ይታያል:: በተለምዶ ለተለያዩ በሽታዎች መፈወሻነት ቅጠላት ይበጠሳሉ፥ ሥሮች ይማሳሉ:: ነገር ግን መድሐኒትነታቸው እንጂ ከምን እንደሚቆረጡና የትና እንዴት እንደሚማሱ እንዲሁም እንዴት እንደሚጠቅሙ ለማንም ሰው ይፋ አይደሉም:: ለማንም ድብቅ ናቸው:: ምንነታቸውና ማንነታቸው ይፋ ከሆነ <u>ይረክሱና</u> የመፈወስ ኃይላቸው ይቀንሣል በሚል ሽፋን ምስጢራቸው አይታወቄ ነው:: ከጥቅም ጋር የተያያዘም ሣይሆን አይቀርም::

2.2.3. <u>አራዊት</u>: በሰው ላይ አደጋ የሚያደርሱ ወይም የሚተናኮሉ እንደ አንበሣ፥ ነብር፥ እባብ፥ ዘንዶ፥ ጅብ ወዘተ...ያሉት እንስሳት (የአካባቢ ልዩነት እንደተጠበቀ ሆኖ) በስማቸው የማይጠሩበት ሁኔታ ያጋጥማል:: በተለይም በጨለማ እነዚህን አስፈሪ ነገሮች መጥራት ወዲያውኑ መጥተው አደጋ ያደርሣሉ ተብሎ ስለሚፈራ በጥቅሉ 'ስም አይጠሬ' በመባል ይታወቃሉ:: በተለይም እባብ በቀንም ሆነ በማታ በቀጥታ ስሙ ሣይሆን <u>ምናምኑ</u>፥ <u>ከይሲው</u> ወይም <u>አውሬው</u> ወዘተ በሚሉት ቃላት ነው የሚጠራው::

እንደ አራዊት ሁሉ ለሰው አስፈሪ የሆኑ እነደ ዛርና እንደ በረዶ ያሉትም የራሣቸው የሆነ ምትክ ስያሜ አላቸው:: ባለዛር ከማለት ባለውቃቢ፥ በረዶ ከማለት የሰማዩ (በገበሬው አንደበት) ማለትን ህብረተሰቡ በተለይም ገበሬው ይመርጣል:: ገበሬው በአዝመራ ወቅት ዝናብን እንጂ ከእሱ ጋር የሚመጣውን በረዶ በጣም ይፈራዋል:: ፍራቻውንም ሲገልፅ "የዘንድሮ አዝመራ ጎተራ አይችለውም ከሰማይ ዳር ያውጣው እንጂ" ይላል::

2.2.4. ድህነት፡ ድህነት እንደሌሎች አስፈሪ ነገሮች ሁሉ በማህበረሰቡ ዘንድ ተወዳጅነት የለውም:: 'ድህነት ያስርባል፥ ያራቁታል፥ ያጎሣቁላል፥ በሰው ፊት ያስገርፋል፥ ስለዚህም በጥብቅ ይፈራል:: እናም የራሱ መግለጫ አለው:: ለምሣሌ ደህ ነው ወይም ለማኝ ነው ከማለት የእኔ ቢጤ ነው:: ራቁት ከማለት ዕርዛት፤ መሸአዳሪ ከማለት የእግዚአብሔር እንግዳ፤ ማለት የተለመደ ነው::

2.3. ጥየፋ፡ ማህበረሰቡ ገሀዳዊ ድርጊታቸውን ወይም ክንዋኔያቸውንና እይታቸውን አጥብቆ የሚጠላቸውና የሚጠየፋቸው በርካታ ነገሮች አሉ:: ብዙዎቹ ሰርንን የሚበጥስ መጥፎ ሽታ ያላቸው ከሰውነት ውስጥ በቆሻሻ መልክ የሚወጡ ናቸው:: ቦታና ጊዜ ተመርጦላቸው እንጂ በገሀድ ወይም በአደባባይ አይወጡም:: ለእይታ ብቻ ሣይሆን ለአንደበትም ስለሚቀፉ ነውርነታቸውን የሚደብቁላቸው ተተኪ ቃላት አሏቸው:: ለምሣሌ ትፋት ከማለት ትውከት፤ ማስመለስ፥ ወደላይ ማለት፥____ ከማለት ተፈጥሮን ማስተናገድ፤ እዳሪ መውጣት (ቀበልኛ) ሽንት ቤት መሄድ፥ ወገብ መፈተሽ/ መሞከር፥____ ከማለት ሰገራ፥ ዓይነምድር፤ ቅዘን ከማለት ሽርተቴ፤ ፈስ፥ ከማለት የዓይነምድር ወላፈን፥ ታችኛ ትንፋሽ፥ ጋስ፤ ንፍጥ ከማለት ተረፈ አንጎል ማለት ነው የሚመረጠው:: እነዚህ የአፀያፊነት ባህሪ ያላቸው ሲሆኑ በሌላ በኩል ደግሞ በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት የሌላቸውና የተጠሉ ተግባሮችና በሽታዎች ከነዚህ ያላነሰ የአስጠያፊነት ደረጃ ያላቸው አሉ:: መሥረቅ፥ ማመንዘር፥ ጉቦ መብላት፥ መስከር፥ በአባለዘር በሽታ መያዝ ወዘተ... ለአብነት የሚጠቀሱ ሲሆኑ እነዚህና ሌሎችም በአደባባይ ተቀባይነት የሌላቸው በጣም ነውር የሚባሉ ሁነቶችና ድርጊቶች ናቸው:: በመሆናቸውም በመደበኛ ስያሜያቸው ሣይሆን በተተኪ ቃላት ይጠራሉ:: ስካር ለማለት ሞቅታ፥ ለብታ፤ ገንዘብ መስረቅ (በመሥሪያ ቤት) ለማለት ገንዘብ መጉደል፤ ጉቦ ለማለት መታያ፥ እጅ መንሻ፤ መሽታ ቤት ለማለት መጠጥ ቤት፤ ሽርሙጥና ለማለት ሴተኛ አዳሪነት፤ ውሽማ ለማለት ቅምጥ፥ ሌብነት ለማለት የእጅ አመል በማለት ይጠቀማሉ::

በአጠቃላይ አፀያፊ ሽታ ያላቸውና ተቀባይነት የሌላቸው ተግባራት በተለያየ መልኩ ሰውን የሚጎዱና የሚያስቀይሙ እንጂ የሚጠቅሙ ባለመሆናቸው አፈጻጸማቸውም ሆነ አጠራራቸው ጠያፍ ነው:: በመሆኑም እንደየሁኔታው በተተኪ ቃላት ይጠራሉ::

2.4 ምላስ አድጥ /tongue twister/ በንግግር ጊዜ ለአንደበት የማይመቹ ከመሆናቸው የተነሣ፥ በተለይ በችኮላ በሚባሉበት ጊዜ የተፈለገውን ሳይሆን ነውር የሆነና ያልተፈለገ ነገር የሚያናግሩ ወይም የሚያሳስቡ ቃላት አሉ:: ህፃናት እንጂ አዋቂዎች እነዚህን ቃላት ሲያዘወትሩ አይታዩም:: ከተጠቀሙም እጅግ ሲበዛ ጥንቃቄ በማድረግ ነፃ ባልሆነ የቋንቋ አጠቃቀም ሥርዐት ይሆናል:: አንዳንድ ምሣሌዎችን ለአብነት እንመልከት:-

ምሣሌ 1 - በቅል ጥሬ ኳኳ - የሚለው በይዘቱ ሆነ በቅርጹ ምንም ዓይነት ነውር ነገር የለበትም:: ነገር ግን በችኮላ በሚባልበት ጊዜ 'በቅል ጥሬ' በሚለው ሐረግ ውስጥ ባሉት በ'ቅ' በ'ጥ' እና በ'ሬ' ተፅዕኖ ምክንያት 'ል' በ'ን' ትተካለች፥ 'ን' ደግሞ 'ቅ'ን ወደ 'ቂ' ለውጥና ሊባል ያልተፈለገ ነውር ነገር እንዲባል ታደርጋለች::

ምሣሌ 2 - በወንፊት ዘር መምረጥ ይህ ሐረግ በዚህ መልኩ ሲታይ ነውር የሆነ እሳቤ የለውም:: ነገር ግን በችኮላ ሲባል ዘር መምረጥ የሚለው ቅንጅት ተገለባብጦ ዘርመጥመጥ የሚል የነውር ቃል ያመጣል::

ምሣሌ 3 - ቀጭን ጠፍር ጠፍታኝ ብዳስስ ተወገቤ ይህ ሐረግ ምላስ አድጥንቱ የሚከሰተው ብዳስስ ተወገቤ በሚለው ሐረግ ውስጥ ባሉት 'ለ' እና 'ተ' ድምጾች ተከታታይነት ምክንያት የሚፈጠረው መስተዋድዳዊ ሀረግ ነውራዊ የሆነ ተግባርን ያሳስባል:: ይህም የሚሆነው ብዳስስ በሚለው ቃል ውስጥ ያለው የመጨረሻ ድምፅ ማለትም 'ስ' እንደ አንድ ጥብቅ ድምጽ ሲነበብ ነው::

ምሣሌ 4 - ቁራ ቆላ ወረደ በዚህም ተናጋሪው የመጀመሪያውን ቃል እንደጠራ ሁለተኛው ቃል ሲጠራ 'ቆ' በማለት ፈንታ በመጀመሪያው ቃል አካሄድ 'ቁ' ስለሚል ያልተፈለገ ቃል እንዲጠራ ያስገድዳል:: ነውር የሆነው የብልት ስም ሊጠራ ይችላል:: ስለዚህ እነዚህን የመሣሠሉ ለአንደበት አስቸጋሪ የሆኑ ቃላት በይዘታቸውም ሆነ በቅርጻቸው የነውር ባህሪ ሣይኖራቸው በአጠራር ጊዜ ያልታሰበ ነውር ነገርን ስለሚያሳስቡ በቋንቋው አጠቃቀም በሩቅ የሚሸሹ ናቸው::

2.5. ነውር መሰል ቃላት: እነዚህ ምላስ አድጥ ከሚባሉት የተለዩ ሆነው ካላቸው የድምፅ ቅንብር የተነሣ ነውር የሆነ ነገር የሚያሣስቡ ናቸው:: ቆላ፥ ቁራ፥ መተኛት፥ መፈለግ፥ ዘር፥ መከፈት፥ ኃጢአት፥ መጥበስ፥ መንፋት፥ ማቀፍ፥ ዳኝነት፥ አያት፥ መገድገድ፥ መኮትኮት፥ ወዘተ...የመሣሰሉት ቃላት ሁሉ አንድም በድምፅ ቅንጅታቸው ወይም በይዘታቸው ነውር ነገርን ያሣስባሉ:: በተለይም ከአውድ ውጭ በተናጠል በሚባሉበት ጊዜ ነውር ነገርን ማሳሰባቸው አይቀርም:: የበለጠ ግልፅ ለማድረግ አንዲት ሴት ወይዘሮ ለአቤቱታ ከዳኛ ፊት ቀርባ የተናገረችውን ለአብነት እንጥቀስ:: አንድ ጎረምሣ በማንአለብኝነት ከሴት ወይዘሮዋ ደጃፍ ላይ ቤት ይሰራል:: ይህን ግፍ ለዳኛ አቤት ስትል፥

"እግዚአብሔር ያሣይዎ አምላክ ያመልክተዎ፤ አቶ እገሌ የተባለ ሰው ከሽንት መሽኚያዬ ላይ ስለገደገደብኝ እንዲነቅልልኝ ስል አመለክታለሁ::" አለች ይላላል::

የተሰመረባቸው ሐረጋት አቤቱታዋን ሌላ መልክ አስይዘውታል:: በመሆኑም ከዚህ ዓይነቱ ስህተት ላለመውደቅ ሲል የቋንቋው ተጠቃሚ በነዚህ ነውር መሰል ቃላት ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጋል:: እንዲያውም አማራጭ ካላጣ በስተቀር አይጠቀምባቸውም ለማለት ይቻላል::

3. <u>ማጠቃለያ</u>፡ ቋንቋ ከሌሎች የመግባቢያ ዘዴዎች በተሻለ መልክ መልዕክትን ወይም ሀሳብን የሚያስተላልፍ መሣሪያ ነው። ሆኖም አጠቃቀሙ ሁልጊዜ ቀልጣፋና ቀጥተኛ እንዳይሆን የልሳነ ማህበረሰቡ ባህል ከፍተኛ ተጽዕኖ ያደርግበታል። እስካሁን በዝርዝር የተመለከትናቸው የአማርኛ ቋንቋ ነውር ቃላት ይህንን በጉልህ ያሳያሉ። ሀሳብን በዋናና ቀጥተኛ በሆነ ስያሜ ከማስተላለፍ ይልቅ በተተኪ ቃላት መጠቀም ወይም መገልገል መልዕክቱን ግልጽ ላያደርገው ይችላል። ከዚህ አንፃር የነውር ቃላቱ በአማርኛ ቋንቋ አጠቃቀምና በራሱ በቋንቋው ላይም የሚያሣድሩት ተፅዕኖ እንዳለ በመገንዘብ ጥናቱ ከሚከተሉት መደምደሚያዎች ላይ ደርሷል።

1. የቋንቋ ህልውና በተጠቃሚው ህብረተሰብ ህልውና ላይ የተመሠረተ ነው ። ተጠቃሚው እስካለና በቋንቋው በሚገባ መጠቀም እስከቻለ ድረስ ቋንቋውም ህልው ይሆናል። ሆኖም ቃላት ነውር ነገርን ስለሚያሳስቡ አገልግሎት እንዳይሰጡ ስለሚደረግ ከጊዜ ብዛት የመረሣትና የመጥፋት ዕጣ ይገጥማቸዋል። ይህም በቋንቋ ዕድገት ብሎም ህልውና ላይ ከባድ ተፅዕኖ ይኖረዋል።

2. በቋንቋ ሣይንስ እይታ ስያሜና ተሰያሚ ወካይና ተወካይ ከመሆን ያለፈ የደምና የሥጋ ዝምድና የላቸውም። የነውር ቃላት አጠቃቀም ግን ይህን እውነታ የሚፈታተን ሆኖ ተገኝቷል - ተሰያሚውን በመፍራት፥ በማክበር፥ በመጥላትና በመጠየፍ ስያሜውንም መፍራት፥ በአጠቃላይ አለመጠቀም በስምና በተሰያሚ መካከል የደምና የሥጋ ዝምድና እንዳለ ከመቁጠር ያለፈ ሊሆን አይችልም።

3. የሰው አእምሮ አሠራር ቀጥተኛና ቀልጣፋ እንደሆነ ይታመናል። በተለይም ከቋንቋ አጠቃቀም አንፃር ነገሮችን ከማስረዘም ማሣጠርን፥ ከዙሪያ ጥምጥም ቀጥተኛ አገላለፅንና አባባልን፥ አለማንዛዛትን ነው የሚፈልገው። ለነውር የሚያገለግሉ ምትክ ቃላት ግን ነገሮችን የመደበቅ፥ የመሸፈን፥ ገሀድ ያለማውጣትና ከቀጥተኛ ይልቅ በዙሪያ ጥምጥም የመግለፅ ተግባርን ያሳያሉ።

## ዋቢ መጻህፍት

Anbessa Teferra.1987 "Ballisha: Women's Speech Among the Sidama," *Journal of Ethiopian Studies*. XX. ( 44-56.)

ደስታ ተክለ ወልድ፥ 1962. *ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት*:: አዲስ አበባ:: አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት

Hudson, R.A. 1980. *Sociolinguistics*. London: Cambridge University press.

Cooper, Robert L 1976. "Sociolinguistics," in: Bender, M.L (ed.). *The Non- Semitic Languages of Ethiopia*. African Studies Center, Michigan State University.

መንግሥቱ ለማ፥ "የአማርኛ ግጥም ዓይነቱ መሠረቱ፥ ሥርዐቱ" *Journal of Ethiopian Studies*, vol. 1-2, 1963.

ሰይፉ መታፈሪያ ፍሬው፥ ውስጠት:: አዲስ አበባ፥ ኮራዝ አሣታሚ ድርጅት፥

Trudgill, Peter. 1974. *Sociolinguistics: An Introduction*. New York: Penguin Books Ltd.

## <u>ዋቢ መፃህፍት</u>

Anbessa Teferra.1987 "Ballisha: Women's Speech Among the Sidama," *Journal of Ethiopian Studies*. XX. ( 44-56.)

ደስታ ተክለ ወልድ፥ 1962. *ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት*:: አዲስ አበባ:: አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት

Hudson, R.A. 1980. *Sociolinguistics*. London: Cambridge University press.

Cooper, Robert L 1976. "Sociolinguistics," in: Bender, M.L (ed.). *The Non- Semitic Languages of Ethiopia*. African Studies Center, Michigan State University.

መንግሥቱ ለማ፥ "የአማርኛ ግጥም ዓይነቱ መሠረቱ፥ ሥርዐቱ" *Journal of Ethiopian Studies*, vol. 1-2, 1963.

ሰይፉ መታፈሪያ ፍሬው፥ ውስጠት:: አዲስ አበባ፥ ኮራዝ አሣታሚ ድርጅት፥

Trudgill, Peter. 1974. *Sociolinguistics: An Introduction*. New York: Penguin Books Ltd.